# ለሚዛን አልባው መፍትሄ

# ቢበጅለት

ሚዛን ገ/ሥላሴ 05-28-18

አልማዝ አፈወርቅ በመገናኛ አካባቢ በትንሽ ሬስቶራንት አምስት ቤተሰብ ከሚያስተዳድሩ ጠንካራ ሴቶች ውስጥ የምትመደብ ናት፡፡ እሷ እንደምትናገረው አብዛኛው ደንበኞቿ በተለያዩ የጉልበት ስራ ተግባራት የተሰማሩና በግንባታ ኢንዱስትሪው ውስጥ በኮንትራት ቅጥር እንደተሰማሩ የሚናገሩ ወጣቶች ናቸው፡፡እሷ የምታቀርበው ምግብ ዋጋው ዝቅተኛና ከተጠቃሚዎች የዕለት ገቢ ጋር የተመጣጠነ በመሆኑ ደንበኞቿ ሁሌም እንደሚያመሰግኗት ትናገራለች፡፡ይሁንና ከዕለት ወደ እለት እየጨመረ በመጣው የሸቀጦች ዋጋ ምክንያት ባለቻት ትንሽ ምግብ ቤት ወደፊት እሷንና ቤተሰቦቿን ለመርዳት መቻሏን ትጠራጠራለች፡፡

አሁን በገበያ ላይ ያለው የምግብ እህሎች ዋጋ በእጅጉ ጨምሯል፡፡የአትክልትና የፍራፍሬ ዋጋም የሚቀመስ አልሆነም ትላለች አልማዝ፡፡ሌላው ቢቀር መብራት ሲጠፉ ደንበኞቿ ራት ለመብላት የሚገለገሉበት ሻማ እንኳን ከአምስትና ስድስት ብር ተነስቶ ከሰሞኑ ወደ ስምንትና ዘጠኝ ብር ደርሷል፡፡በዚህ ሁኔታ የኑሮ ውድነቱ የመጨረሻ መቆሚያ የት እንደሚሆን መገመት አልቻለችም፡፡ምንአልባት መንግስት ጣልቃ ቢገባና ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ሸቀጦችን በቅናሽ ዋጋ በየአካባቢው ማቅረብ ቢጀምር ገበያው መረጋጋት እንደሚጀምር ታስባለች፡፡

ይሁንና የነገን ቀርቶ የዛሬን በአግባቡ የማያስቡና ህዝብን ለማወናበድ የተዘጋጁ ስግብግብ ነጋዴዎች በየጥጋጥጉ በተሰገሰጉበት አገር ህብረተሰቡ ራሱ መፍትሄው አካል ካልሆነ የመንግስት ማስተካከያ ብቻውን የት ያደርሳል የሚሉ አስተያየት ሰጪዎችም አሉ፡፡እንደነሱ አስተያየት የመንግስት ማስተካከያ ብቻውን ወደማያባራ የኢኮኖሚ ቀውስና አዙሪት ውስጥ የሚጨምር ነው፡፡ስለዚህ መሆን ያለበት ከተቻለ አቅርቦትን ማብዛትና የተትረፈረፈ ማድረግ፣የግብርና ምርትን ማሳደግ ከዚህ አልፎ ደግሞ ተጠቃሚው ራሱ ስግብግብ ነጋዴዎችን በመዋጋት መብቱን እንዲስከብር ማድረግ የተሻለ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

ከዚህ ጋር በተገናኘ ከሰሞኑ የወጣው የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ፣ ከሚያዝያ ወር ባለሁለት አሃዝ የግሽበት መጠን ያልተለየ እንደሆነ ያሳያል፡፡ይህ ስታትስቲካዊ ስሌትንና ንጽጽርን መሠረት ያደረገ አሐዝ ነው፡፡ ይሁንና ገበያው ግን ከተጠቀሰውም በላይ የዋጋ ለውጥ የሚታይበት ነው፡፡ የኤጀንሲው መረጃ እንዳለ ሆኖ፣ በተጨባጭ የምናየው እውነታ አሳሳቢ የዋጋ ለውጥ በየጊዜው እየታየ ስለመሆኑ የሚጠቁም ነው፡፡በአሁኑ ወቅት በአብዛኛዎቹ ምርቶች ላይ እየታየ ያለው የዋጋ ዕድገት ህዝቡ ያለውን ገቢና አገሪቱ ያትን ዕድገት ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ፈጣን የዋጋ ለውጦች በበርካታ ምርቶች ላይ እየታየ በመሆኑ የገበያውን በአቅርቦትና በፍላጎት የመመዛዘን ጤናማነት ላይ መመስረት ያጠራጥራል፡፡

ገበያው ላይ የሚታየው የሸቀጦች ዋጋ የመለዋወጥ መጠንና ፍጥነት እያሻቀበ በመሆኑ፣ ኅብረተሰቡ ለዕለታዊ ፍጆታው የሚጠቀምባቸው ምርቶች ብቻም ሳይሆኑ፣ የግንባታ  ግብዓቶችን የመሳሰሉ ምርቶችም የሚያሳዩት የዋጋ ለውጥ በየአቅጣጫው እየሰፋ መሆኑን ያመለክታል፡፡ለአብነትም በብረትና በሲሚንቶ ዋጋ ላይ የተደረገ ቅኝት እንደሚያሳየው በቅርቡ ሁነኛ መላ ካልተፈለገለት አሁን ያለው የዋጋ ንረት ችግር እያበበ ያለውን የግንባታ ኢንዱስትሪ ሊያስተጓጉለውና ጨርሶም ሊያስቆመው ይችላል፡፡ በቅርቡ ይፋ የተደረገ አንድ ጥናት እንዳመለከተው፣ ብረትን ጨምሮ ሌሎች ለግንባታ ሥራዎች የሚውሉ ግብዓቶች የውጭ የምንዛሪ ለውጡ ከተደረገበት ከጥቅምት ወር ወዲህ በአማካይ ከሃምሳ በመቶ በላይ የዋጋ ጭማሪ አሳይተዋል፡፡ ይህ ጥናት እስከ ጥር ወር 2010 ዓ.ም. ያለውን መረጃ ተመርኩዞ የተሠራ ሲሆን፣ ከዚያም በኋላ የተደረገው የዳሰሳ ጥናትም ቢሆን፣ በዘርፉ የታየው የዋጋ ጭማሪ ከዚህም በላይ እንደሆነ አመላክቷል፡፡

እንደ ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ሁሉ መሠረታዊ የሚባሉ ምርቶች ዋጋም እየጨመረ መምጣቱ አሳሳቢ ሆኗል፡፡ እየታየ ያለው የዋጋ ጭማሪ ተገቢ እንዳልሆነ የሚያመላክቱ መረጃዎች ቢኖሩም፣ በርካታ በአገር ውስጥ እየተተመረቱ የሚቀርቡ ምርቶች ግን የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ሰበብ በማድረግ ዋጋ እየተጨመረባቸው መገኘቱ ነገሩን በአንክሮ ለተመለከተ ግራ የሚያጋባ ነው፡፡ ምክንያቱ ተገቢነት ይኖረውም አይኑረው፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚታየው ተደራራቢ የዋጋ ጭማሪ ግን መጨረሻው የአብዛኛውን የኅብረተሰብ ክፍል ህልውና  እንደሚፈታተነው የታመነ ነው፡፡ የዋጋ ጭማሪው በቀናት ልዩነት ውስጥ መታየት መጀመሩ ብቻም ሳይሆን፣ ይብሱን እየሰፋ መምጣቱ ለከፋ የኑሮ ውድነት የሚዳርግ አካሔድ ውስጥ እየገባ ነው ወደሚለው መደምደሚያ ያደርሳል፡፡

እየታዩ ያሉት የዋጋ ጭማሪዎች የሕዝብን ብሶት ሊቀሰቅሱ የሚችሉበት  አጋጣሚ ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ከዚህ አኳያ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች የዋጋ ግሽበቱ ጉዳይ ችላ መባል የለበትም በማለት እየተናገሩ ይገኛሉ፡፡ ገበያው የተወጣጠረበት ምክንያት ምን እንደሆነና ዋጋዎች ያለማቋረጥ የሚንሩበትን መንስዔ በትክክል በማጤን የመፍትሄ እርምጃ ሊሆን የሚችል የማስተካከያ ስራ መስራት ደሀውን ሸማችና ህዝብ ከምሬት እንዲጠበቅ ያስችላል፡፡ አሁን ባለው የገበያ ሁኔታና የኑሮ ውድነት አካሄድ ምንም ዓይነት የሸቀጦች ዋጋ ድጎማ፣የገቢ ማስተካከያ ወዘተ ያልተደረገለት የኅብረተሰብ ክፍል እየጋለበ ካለው የዋጋ ጭማሪ ጋር መራመድ ወደማይችልበት ደረጃ አድርሶታል፡፡ ለአብነትም የዚህ ጽሁፍ ጸሀፊ ካለሁበት የመገናኛ መንደር ከስራ ስመለስ እንደወትሮው ሁሉ ከኪዮስኮች የምገዛው ወተት አስቀድሞ አለቀ ይባላል፡፡ ይህም ለሳምንታት ተደጋግሟል፡፡ አለ ከተባለም የግማሽ ሊትር ወተት ወደ ሃያ ብር አሻቅቧል፡፡በአጭር ጊዜ ልዩነት ውስጥ የምግብ ምርቶች ዋጋ ለምን እንደዚህ ሊወደድ እንደቻለ ማንም መልስ ሊሰጥ አልቻለም ወይም ለምን ይህንን ያህል ዋጋው ናረ ብሎ ገበያውን ለማጣራት የደፈረ የለም፡፡

የሌሎች ሸቀጦች ዋጋ ማሻቀብም የትየለሌ ነው፡፡ምስር፣ጥራጥሬና ሸንኩርት በአጠቃላይ ደሃው ሕዝብ እለት ከእለት የሚመገባቸው ምርቶች ሁሉ ያላቸው የዋጋ ንረት በቃላት የሚገለፅ አይደለም፡፡ ይህንን ከባንክ የብርና የዶላር ምንዛሬ ማስተካከያ ማግስት ተደረገውን ለውጥ ተከትሎ የመጣውን ውድነት ማንም ማሰብም ሆነ መጠየቅ አይፈልግም፡፡ የዋጋ ጭማሪው ከላይ እስከ ታች ያለውን የኅብረተሰብ ክፍል የሚሸነቁጥ በመሆኑ  ለብዙኃኑን ‹‹ኧረ ወደየት እየሄድነው?›› በማሰኘት ላይ ነው፡፡ እንደአንዳንዶቹ ገለጻ መንግሥት አገር ለማረጋጋትና አንድነትን ለማጠናከር እያደረገ ባለው ጥረት ስለተወጠረ ገበያውን ለማረጋጋት፣ኢኮኖሚውንና የንግዱን ዘርፍ መስመር ለማስያዝ ያደርግ የነበረውን እንቅስቃሴው ገድቦታል፤ የሚሰጠውንም ትኩረት ቀንሶታል ይህም የኢኮኖሚው ጉዞ የቁልቁለት መንገድ እያደረገው መጥቷል፡፡በመሆኑም አዲሱ የመንግሥት አስተዳደር ይህንን ጉዳይ በጥልቀት በመፈተሽ መፍትሔ ሊያበጅለት ይገባል የሚለው ጥሪ የብዙኃን እየሆነ የመጣ ይመስላል፡፡

በተለይ መሠረታዊ ምርቶችና ሸቀጦች፣ ያውም በመንግሥት ይደጎማሉ የሚባሉትና እንደ ስንዴ ያሉት የምግብ ሸቀጦች በተፈለገው መጠን አለመገኘታቸው ሳይበቃ ለዋጋ ጭማሪ መባባስ ምክንያት ሆነዋል፡፡ በመሆኑም እንደ ፖለቲካው ሁሉ የሁሉም ነገር መሰረትና አንቀሳቃሽ ለሆነው የኢኮኖሚ ዘርፍም  ልዩ ትኩረት ይሰጠው ዘንድ የግድ ይላል፡፡

በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዓብይ አህመድ ማክሰኞ ግንቦት 7 ቀን 2010 ዓ.ም. ለከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በጽሕፈት ቤታቸው ባደረጉት ገለጻ አንድ ያወሱት ቁምነገር ነበር፡፡ ‹‹ኢትዮጵያ እያደገች ናት፣ ነገር ግን ኢትዮጵያ አድጋለች ከማለት ባሻገር ሕዝቡ ምን ያህል ተጠቅሟል የሚለውን መፈተሽና ማረጋገጥ አለብን፤›› በማለት አንኳርና አንገብጋቢ ጉዳይ ተናግረዋል፡፡ የአገሪቱ ኢኮኖሚ የሚያመነጨው ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ለአገሪቱ ሕዝብ የመዳረሱ ጉዳይ መቼም ቢሆን ችላ የሚባል ጉዳይ አይደለም፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ግን አፅንኦት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ዋነኛ ጉዳዮች መካከል የግብይት ሥርዓቱ አንዱ ሲሆን፣ በሌላ በኩል አጠቃላይ የኢኮኖሚው ይዞታ ነው፡፡

የኢኮኖሚውን ጉዳይ በርዕሰ ጉዳይነት አንስቶ ለመነጋገር ሲፈለግ ደግሞ፣ ከሕዝቡ የዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ካላቸው መሠረታዊ አቅርቦቶች መነሳት ተገቢ ነው፡፡ በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ ወሳኝ ሚና ያላቸው ሸቀጦች እጥረትና የዋጋ ግሽበት ሥጋት እየፈጠረ ነው፡፡ በግሽበቱ ምክንያት የአገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገቱን የሚያስተጓጉሉ ችግሮች ከፊቱ እየተጋረጡበት የመጡም ይመስላል(ለምሳሌ ሥር የሰደደ የውጭ ምንዛሪ እጥረት)፡፡ ይህ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለኢኮኖሚው መቀዛቀዝና መድከም ምክንያት ከመሆኑም በላይ፣ በጥናት ላይ የተመሠረተ አስቸኳይ ዕርምጃ ካልተወሰደ አምራች ኢንዱስትሪው ሙሉ በሙሉ ቀጥ ሊል ይችላል የሚል ሚረት አዘል ትንበያዎች ሁሉ አሉ፡፡

በመሆኑም መንግሥት ይኼንን ሥር የሰደደ ችግር በመረዳት አገር የሚያከስሩና የማያዋጡ ፕሮጀክቶች ካሉ እነሱን በመፈተሽ መቀነስ፣ማዘግየት ወይም የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ ይህንን ካደረገ በሕዝብ ላይ ኢንቨስት የማድረግ አቅሙን ይጨምርለታል፡፡ በተጨማሪም ገበያው ላይ ውዥንብርና ምስቅልቅል የሚፈጥሩ ሕገወጥ ደላሎችንና ኮንትሮባንዲስቶችን በመከታተል ማስቆም የግድ ነው፡፡ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ለአገር ውስጥ ግብይት መዛባት ዋነኛ ምክንያቶች የሚባሉት ገበያው ውስጥ ተደራጅተው የሚገቡ ሕገወጦች የግብይት ሥርዓቱን እያፋለሱት እንደሆነ ሲነገር ቆይቷል)፡፡

በመሆኑም መንግስት ገበያን ለማረጋጋት ያለውን ጉልህ ሚና በአግባቡ መጫዎትና ህዝቡን ከስቃይ የአገርንም ኢኮኖሚ ከውድቀት መታደግ ይኖርበታል፡፡ከዚህ ጎን ለጎን ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በመፈተሽ መሠረታዊ ለውጥ ማድረግም ተገቢ ነው(ልብ ያለው ልብ ይበል ከፈረንሳይ አብዮት ጀምሮ

የሕዝብን ብሶት ሲቀሰቅስ የሚታየው ዋና ጉዳይ የኢኮኖሚው ቀውስ እንዲሁም እሱን ተከትሎ የሚመጣ የማህበራዊ ቀውስ ነው)፡፡ ለብርቱ በሽታ ብርቱ መድሃኒት ማዘዝ ተገቢ ነው፡፡